የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 52
ADDIS ABABA 30th June. 2005

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፪/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ከቱርክ ሪፐብሊክ ጋር የተደረገው የባህል፣ የትምህርት፣ የሳይንስ የመገናኛ ብዙሀን፣ የወጣቶችና የስፖርት ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፩፻፷፯

CONTENTS

**Proclamation No. 462/2005**

Agreement on Culture, Education, Science, Mass Media, Youth and Sports Cooperation with Republic of Turkey Ratification Proclamation Page 3167

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፪/፲፱፻፺፯

## በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገውን የባህል፣ የትምህርት የሳይንስ፣ የመገናኛ ብዙሀን፣ የወጣቶችና የስፖርት ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በቱርክ ሪፐብሊክ መካከል የባህል፣ የትምህርት፣ የሳይንስ፣ የመገናኛ ብዙሀን፣ የወጣቶችና የስፖርት ትብብር ስምምነት ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም አዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ከቱርክ ሪፐብሊክ ጋር የተደረገው የባህል፣ የትምህርት፣ የሳይንስ የመገናኛ ብዙሀን፣ የወጣቶችና የስፖርት ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፪/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 462/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT ON CULTURE, EDUCATION, SCIENCE, MASS MEDIA, YOUTH AND SPORTS COOPERATION WITH THE REPUBLIC OF TURKEY

**WHEREAS,** the Agreement on Culture, Education, Science, Mass Media, Youth and Sports Cooperation between the Federal Democratic republic of Ethiopia and the Republic of Turkey was signed in Addis Ababa the 25th day of June, 2004;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30th day of June, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement on Culture, Education, Science, Mass Media, Youth and Sports Cooperation with Republic of Turkey Ratification Proclamation No. 462/2005."

## ፪. የስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና በቱርክ ሪፐብሊክ መካከል ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የባህል የትምህርት፣ የሳይንስ፣ የመገናኛ ብዙሀን፣ የወጣቶችና የስፖርት ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. ስምምነቱን በሥራ ላይ የማዋል ሥልጣን

ይህን ስምምነት በየሥልጣን ክልላቸው በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር፣ ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር እና ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement on Culture, Education, Science, Mass Media youth and Sports Cooperation signed in Addis Ababa on the 25th day of June, 2004 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Republic of Turkey is hereby ratified;

## 3. Power of Implementation

The Ministry of Youth, Sports and Culture, the Ministry of Education, the Ministry of Information and the Science and Technology Commission are hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement in their respective jurisdictions.

## 4. Effective Date

The Proclamation shall enter into force on the 30th day of June, 2005.

**Done at Addis Ababa, the 30th day of June, 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት